**ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ**

**Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity**

Efdpu@aol.com www.Finote.org


በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በ ጥር 14 ቀን 2011 ዓም የተላለፈ ሐተታ

# አቅጣጫውና ግቡን ያላወቀ ለውጥ ከንቱ ነው

በሀገራችን ለመሰረታዊ ለውጥ ሲካሄድ የነበረው ሕዝባዊ ተደናቅፎ በባእዳን ድጋፍ የይስሙላ ለውጥ ሂደት ከተጀመረ ወራትን አስቆጥሯል። ሕዝብ የሚጠበቀውን ጉጉትና ፍላጎት ለሟሟላት ገና አልተሳካለትም ብሎ መደምደሙ ምክንያታዊ ነው ማለት ግን ይከብዳል ። ዘመናትን ያስቆጠሩ ሀገራዊ ችግሮችን በወራት ቀርቶ በዐመታት ለማስወገድ ፤ የበርካታ ኃይሎችንና የመላውን ህዝብ ትብብርንና ንቁ ተሳትፎን ይጠይቃል ። ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን መገንባት ከወሳኞቹ ጉዳዮች የመጀመሪያውን ረድፍ ይይዛሉ። እነኝህን ሁሉ በግምት ወስጥ ማስገባት ለሚታሰበው ዐላማ ስኬታማነት ዋስትና ይሆናሉ።ከሁሉ በፊት ግን የዴሞክራሲ ግንባታ የቅድሚያ ቅድሚያ ጉዳይ ሊሆን ይገባል ። እነኝህን ወሳኝ ጉዳዮች ታሳቢ አድርጎ መንቀሳቀስ አማራጭ አይኖረውም ።

የዴሞክራሲን መሠረት መጣል ተሳትፎንና ድጋፍን የሚያረጋግጥ ሲሆን የሕዝብ ሙሉ ተሳትፎ ውጤት ሊያስመዘግብ የሚችለው ደግሞ፤ ዴሞራሲያዊ ተቋማቱ ነፃና ገለልተኛ ሆነው ሲመሰረቱ ብቻ ነው። ህዝብን መሰረት ያደረገ ስር ነቀል ለውጥ እንዲመጣ ከተፈተለገ ደግሞ የወደፊቱን አቅጣጫ ሊያመላክት የሚችል በግድ አቅጣጫና ግብን መቀየስና በተግባር መተርጎም ያስፈልጋል። ይኽ ጉዳይ ፤ አከራካሪ ሊሆን አይችልም ።

አቅጣጫና ግብን ለመቀየስ ደግሞ የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በሚገባ መረዳትን ይጠይቃል። ይህ **መኖር አለበት ስንል ህዝብ የስልጣን ምንጭ የሚሆንበትን ዓላማ በግልጽ አስቀምጦ ወደ ግቡ የሚወስዱትን ሂደቶች እየተቆጣጠሩ ዘላቂ ግቡ እውን እንዲሆን ማድረግ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ አሁን ለህዝብ ግልጽ ሆኖ ይታያል ማለት አይቻልም ።**

የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ችግሮች በቅጡ ያልተገነዘበ ማነኛውም ኃይል፤ የስር ነቀል ለውጥ ሂደትን መቀበል ይቸግረዋል። ውስብስብ የሆነውን የሀገሪቱን ችግር ሳይረዱ ፤ መፍትሄ ማግኘት ያስቸግራል። በዚህ ምክንያት ነው ያገራችንን ችግር ለመፍታት ያልተቻለው። ሕዝባዊው ለውጥ ፤ የተሳካለትን የሽግግር ጉዞ እንዳይራመድ መሰናከል የገጠመውም አንደኛው ምክንያት፤ ይኽ ይመስላል ። የሀገሪቱ ችግሮች፤ ድርብ ድርብር ፤ ውስብስብና ውጥንቅጥ፤ ጥልፍልፍና መላ ቅጡ የጠፋበት ነው። የመፍትሄው ፍለጋ ሂደት፤ በሆይ ሆይና በውቂው -ደብልቂ ፤ በግርግር፤ በያዘው- ልቀቀውና በመደነባበር የሚፈታ አይደለም ። በረጋ መንፈስ፤ አስተውሎና አርቆ በማሰብ ሊስተናገድ ይገባል። የሰከነ አዕምሮን አንግቦ መንቀሳቀስ፤ ዘለቄታው የተሳካ ይሆናል ። እወደድ ባይነት ብቻውን ሩቅ ምዕራፍ አያስኬድም ።

የህዝብን ፍላጎትና ጥያቄ ማስተናገድ የሚቻለው ፤ በህዝብ ወገንተኝነት እንጅ፤ ህዝበኝነት (ፖፐሊስት ) በመሆን አይደለም። በመፈክር ንባቤ ሀገር አይገነባም ። በአደባባይ ጠርሙስ በመስበር የሕዝብን ልቦና አዕምሮ ማስተናገድ

አንዳልተቻለ ካለፈ ታሪክ መማር ይገባል ።ሀገርና ሕዝብ አደጋ ላይ ሲወድቁ ፤ እግሬ አውጭኝ ብሎ በአሳፋሪ ሁኔታ መሸሽ ፤ ለተተኪው ትውልድ አንገት ሰባሪ ታሪክን ጥሎ ማለፍ እንጅ ፤ መልካም ቅርስ አይሆንም። ህዝብና መንግሥት፤ አንድ ካካል አንድ አምሳል ሆነው ካልተሰለፉ፤ ሀገር ባለቤት ታጣለች። ባለቤት ያጣ ሕዝብና ሀገር የማንም መጫወቻ ሆኖ ይቀራል። የዛሬይቷ ሀገራችን በዚህ ሁኔታ ላይ ትገኛለች ብሎ መደምደም ከዕውነት የራቀ አይደለም ።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በርካታ ውስብስብ ችግሮች ተደቅነውባታል

**አንደኛ** ነገር ፤ዜጎቿ እንደ ዜግነት ክብርና ምልዑነት ሳይሆን ፤ በዘርና በቋንቋ፤ ፍርክስካሽ ተመድበው እንዲታዩ በመሆናቸው ነው ። ይኽም ሁኔታ ዜግነታቸው ብቻ ሳይሆን፤ ሰብዕናቸውንም ጭምር አዋርዶታል ።

**ሁለተኛ** ነገር ፤ መልክዓ ምድሯ፤ በምልዑነት ሳይሆን፤ በፍርክሥክሥነት / በክልልነት ተጨማትራ እንድትታይ ተደርጋለች ። አዲሱ ትውልድ፤ ሀገሩን የሚያያት ፤ በኢትዮጵያነቷ ሳይሆን ፤ በፍራክሽን ሂሳብ አግባብነት ሆኗል ። ኢትዮጵያ ተብላ ትጠራ አትጠራ፤ ኢትዮጵያ ትኑር/ አትኑር ደንታ እንዳይሰጠው ሆኖ እንዲያድግ እየተደረገ ትውልድ ሆኗል ። ክልል፤ ለአንድ ሀገር ዜጎች መኖሪያ ሳይሆን ፤ ለክብት ግጦሽ ማሰማሪያ፤ መናሃሪያና ማጎሪያ ቦታ ነው ። ሀገር እንደ ሀገር ፤ መቆጠሯ እየቀረ፤ በየክልሉ ተኮድኩዳና ፤ ተደይና እንድትቀር ተፈርዶባታል ። ይኽንን ያደረጉት ባለ ስንኩል አዕምሮዎቹ የዘረኛ አገዛዝ አራማጆች ወያኔዎቹ ናቸው ። አሁን ግን፤ በሕዝባዊው ዓመፅ ዋጋቸውን እየከፈሉ በመክሰም ሂደት ውስጥ ይገኛሉ ። ለዚህም፤ ወጣቱ ትውልድ ምስጋና ይድረሰው ! **ከባድ መሥዋዕት ከፍሏልና !**

**ሦስተኛ** ነገር ፤ መንግሥት የሚባለውን መስፈርት የሚያሟላም ሆነ ሥልጣኑን ከህዝብ የተቀበለ ተቋም በሀገሪቱ ውስጥ የለም ። ህጋዊነትም የሕዝብ ተቀባይነት ያለው ኃይል የለም። ሀገሪቱን እንደ ሀገር ፤ ዳር ድንበሯም ፤ የግዛት ልዋላዊነትም ሆነ ዜጎቿንም እንደ ዜጎች፤አዋኅዶና አስከብሮ ያለ መንግሥታዊ ተቋም ይታያል ለማለት አያስደፍርም።

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጥል እንዳትችል ያደረጓት ዘረኞች ጥንታዊቷንና ታሪካዊነቷን እንደ ሀገር እያጠፉ ፤ ወደ ዘመነ-መሳፍንት የጉልት መንደር እንድተገባ ለማድረግ እየተወራጩ ይገኛሉ ። የጦር አበጋዞችና ያካባቢ ታጣቂ ነፍጠኞች የየግላቸውን ግዛትና የአገዛዝ ሥርዓት እያሰፉኑ የአገሪቱን ህልውና አደጋ ውስጥ እንዲወድቅ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ አገሪቱ በአሁኑ ወቅት ብዙሃን ባለነፍጥ ወጠጤዎች የሚደነፉባት መሬት በመሆኗ ፤ ማን እንደሚቆጣጠራትና ወደ የትስ አቅጣጫ እንደምትሄድ እንኳ ማንም ወገን ሊያውቅ ከማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል ። አካሄዱ፤ ፍኖተ- ካርታ ( ሮድ ማፕ) ስሌለው፤ ህዝብ ግራ ተጋብቷል። የባሰ እንዳይመጣ ከመጨነቅ ሌላ ምርጫ አጥቷል ።

**" ለኢትዮጵያ ሕዝብ፤ የአንድ መቶ ዐመት የቤት ሥራ እንሰጠዋልን። "** ብለው ያሰቡት ዕቅድ በተግባር እየታየ ነው ። ይህንን ትንቢት በተግባር ለመፈፀም አሁን ሥልጣኑን የተረከበው የአገዛዝ ቡድን፤ አውቆም ይሁን ሳያውቀው ሀላፊነቱን ወስዷል። በእነርሱ አመለካከት፤ ኢትዮጵያን ማዘመን ማለት፤ ወደ 18ተኛው ክፍለ ዘመን እንደ ነበረችበት የጨለማ ዘመን የኋላ ዞር ጉዞ ማስኬድ ሆኗል ። ሀገርን እንደ ኩበት ጠፍጥፎ መስራት ቀላል የሚመስላቸው የዘረኛ አገዛ አራማጆች ፤ በቀላሉ በማይበጣጠሰውና በብዙ ክርና ማግ የተዋሃደውን የህዝብ አንድነት ለማፍረስ ላለፉት ሃያ ሰባት ዐመታት ሞክረው ነበር ። ሳይሳካላቸው ቀርቶ፤ እነርሱም ፤ እንደ ዮዲት ጉዲት ፤ እንደ ግራኝ መሃመደና እንደ ደርቡሾች መና ሆነው ቀርተዋል ።

አሁን በሥልጣን ላይ የሚገኙት የወያኔ ቅሪቶች፤ " **ከታሪክ ያልተማረ፤ ራሱን ሲረግም ይኖራል "** እየህነባቸው ነው። በስልጣን ላይ ያሉት አዲሶቹ ሹሞች የሽግግር ስምሪት አቅጣጫ ለመስጠትና ሕዝባዊው ኃይል እንዲያገኝና የታሰበውንም ግብ እንዲመታ ለማድረግ መሠረታዊ የሆነ የሥርዓት ለውጥ የሚገኝበትን ሁኔታ ከማመቻቸት ይልቅ በጥገና ለውጥና ፤ በአዝጋሚና ተንፏቃቂ ማጥ ውስጥ እየዳከሩ ይገኛሉ።

ዞሮ ዞሮ፤ ለዘላቂ ሠላምም ሆነ ለአስተማማኝ የለውጥ ሂደት የሚከተሉት ጉዳዮች መረጋገጥ ተፈጥሯዊ ነው ተብሎ ይታመናል ።

**1ኛ.** ሀገራችን መሠረታዊ የሆነ የሥር ዓት ለውጥ እንጅ የጥገና ለውጥ አያስፈልጋትም። አሁን ላለው ሀገራዊ ችግር መንስዔው ፤ በውሸት ትርክትና በቋንቋ ላይ የተመሰረተው ህገመንግሥት ተብየው የወያኔ ፕሮግራም ሰነድ ነው። ይኽ ህገ መንግሥት ላንዴና ለመጨረሻው ወወገድ አለበት ። አሁን በየቦታው የሚካሄደው የእርስ በርስ የዜጎች ፍጅት ፤ መሠረታዊ ምክንያቱ ወያኔ የፈጠረው የክልል አገዛዝ ነው። ይህ ጠንቅ ደግሞ በዘር ላይ የተገነባው ህገመንግሥቱ የፈጠረው በመሆኑ፤እርሱ ካልተወገደ በቀር ፤ ዜጎች በሠላም አብረው እንደወትሯቸው ለመኖር አይችሉም።

**2ኛ.** መርዘኛውን ህገመንግሥት የቀረፀው ይኽ ጠንቀኛ ዘረኛው ሥርዓት በመሆኑ፤ እንደ ሥር ዓት፤ እስከ ጣጣው ካልተወገደ፤ ስር የሰደደው የሀገሪቱ ችግር ይወገዳል ማለት ዘበት ነው ። በመሆኑም፤ መሠረታዊ የሥር ዓት ለውጥ እንጅ፤ ለጥገና ለውጥ ጊዜና ሃብት ማባከን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደመክዳት ይቆጠራል።

**3ኛ.** በሀገሪቱ ሠላምና መረጋጋት መምጣት የሚችለው፤ በየደረጃቸው ቅደም- ተከተል ፤ ሦስት ጉዳዮች ዕውን ሲሆኑ ብቻ ነው። እነርሱም :-------

**ሀ.** ዴሞክራሲ በመላው ሀገሪቱ ሲሰፍና ዜጎቿም ያለቅድመ ሁኔታ ተጠቃሚና ሙሉ ተሳታፊ ሲሆኑ ነው።

**ለ.** የሽግግር ወቅት ፤ ከሙሉ ኃላፊነቱና ግዴታው፤ ተግባሩና ዕድሜው በህዝብ ስምምነት ህጋዊነቱ ተረጋግጦ ሲታዎጅ ነው።

**ሐ.** የሀገሪቱ ዜጎች፤ በወኪሎቻቸው አማከኝነት የተዘጋጀውን የሕገመንግሥት ረቂቅ ፤ በሕዝበ-ውሳኔ (ረፈረንደም) ከጸደቀ በኋላ ፤ በዜጎች ቀጥታ ተሳትፎ በሚመጣ ምርጫ፤ ዴሞክራቲክ መንግሥት ሲቋቋም ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን፤ ከላይ በቅደም ተከተል በሰፈሩት ሂደቶች ካላለፈች በስተቀር ፤ በጥግና ለውጥ ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት ፤ ታገኛለች ተብሎ አይታሰብም ። ለዘላቂ ሠላምና መረጋጋት፤ ይህንንም ዕውን ለማድረግ የሚያስችለውን መሠረታዊ ለውጥ ከሚፈልጉ ጋር ተባብሮ ለመስራት ጥሪያችንን እናስተላልፋለን ።
በሌሎች ድግስ ሄዶ ፍርፋሪ መጠየቅ፤ ቡኩርናን ፤ በጭብጥ ምስር መለወጥ ስለሚሆንብን ፤ያንን አናደርገውም! የምንታገልበት መርሆም አይፈቅድም !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !
ጸረ ወያኔ ጸረ ኢሕአዴግ ትግላችን ተፋፍሞ ይቀጥል !!